# የኢትዮጵያ ሊቆች!





ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ ጠቢብ ኢንጂነሮች. . .
ባለ ሁለት ዲግሪ፣ ባለ"ሦስት" እውቀቶች፣
ባለም ዙሪያ ያላችሁ እናንት የ"ጨው ዘሮች"...!

እስኪ ተሰብስቡ ባንድጋ ምከሩ፤
የኢትዮጵያን ዕጣ እድሏን ቀምሩ፤
"ሙጃሌ" ለማውጭያ፣ ለእሾኽ መመንገያ...
እስኪ "መርፌ" ስሩ!





እናንት ምሁራን የኢትዮጵያ ሊቆች፤
መሰረተ-ግኝት የገበሬ ልጆች፤
እስኪ ላባታችሁ ማረሻ ስሩለት!
እስኪ ለናታችሁ ወፍጮ ትከሉላት!



ከግል ጥቅም ዝና ከወረት ባሻገር፣
እስኪ ጥቂት ጊዜ ከፍላችሁ ለአገር፣
የእውቀታችሁ ውጤት መላችሁ ይሰንዝር!

በፈረንጅ መጽሔት የወጣው ዝናችሁ፣
እናንት የጭቁን ልጅ፣ መነሻ ቤታችሁ...
አዝማለችና... ሳትፈርስ በሕይወት፣
በዚህ ጭንቅ ጊዜ ቶሎ ድረሱላት፤
ከመቀመቅ ጉዞ ከጥፋት አድናት!






ሊቀ-ሊቃውንቶች አንቱ  የተባላችሁ፣
በገበሬው ግብር ለዚህ የበቃችሁ፣
እስኪ ለአንድ አፍታ አስቡት ያንን ሕዝብ፣
በረሃብ፣ በስቃይ፣ ባምባገነን ጡጫ በግፍ ሲደበደብ...፤
"የናቴ መቀነት ጠልፎኝ ነው" ሳትሉ፣
ለፍትህ፣ ለእድገት... እስኪ መላ በሉ!



"ኦክስፎርድ"፣ "ሐርቫርድ"፣ የ"የል". . . ምሩቃን፣
ባለማረግ ጀግኖች እናንት ሊሂቃን፣
ዕድሜ ልካችሁን ባዕድ ስትገነቡ፣
ከገበሬው ጎጆ ጠልቃችሁ ሳትገቡ፣
ምን ተብሎ ይጻፍ? ሕይወት ታሪካችሁ፣
መጪው ምስኪን ትውልድ እንዴት ያስታውሳችሁ?!



በሣይንስ ቅምራ በሂሳብ ስሌቱ፣
በዕደ-ጥበብ ዘርፉ በምጣኔ ሃብቱ...፣
የባዕድ ጎተራ ጥቅጥቅ የምትሞሉ፣
ለእማማ ኢትዮጵያም እስኪ መላ በሉ!

ጌታቸው አበራ
ሐምሌ 1999 ዓ.ም.